ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ሲያጋጥሞት እና ተከስቶ ሲመለከቱ ለማን ሪፖርት ያደርጋሉ?

ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ሲፈፀም ጥቃቱ የደረሰበት ወይም ጥቃቱ ሲፈፀም ያየ ሰው በአቅራቢያው ላለ የህግ ወይም የፍትህ አካል ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ከዚህም በተጨማሪ በሚከተሉት ቁጥሮች በመደወል ማሳወቅ ይችላሉ፡፡

6388 አለኝታ ድምፃችሁ ይሰማል ! (ሴታዊት)

የአለኝታ የምክር፣ የህግ ድጋፍና የማረፊያ አገልግሎቶች ዝርዝር ማውጫ በ https://setaweet.com/wp-content/uploads/2022/07/Alegnta-Hotline.pdf ላይ ይገኛል፡፡

የህግ ድጋፍ እና ማማከር አገልግሎት ለማግኘት - 7711

የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር

+251-115508783

+251-115509256

የሴቶች ማረፊያ እና ልማት ማህበር

+251-9-11-76-80-52

+251-1-16-67-22-90

ፆታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫዎች

በጋንዲ፣ዳግማዊ ምኒሊክ፣ ጥሩነሽ ቤጂንግና ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታሎች ይገኛሉ።

ለተጨማሪ መረጃ

አድራሻ፡ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት (ኢ.ሴ.ማ.ቅ)

ስልክ፡-+251118217758/59

ፖስታ፡- 19357

ማህበራዊ ሚዲያ፡-

www.facebook.com/newa.ethiopia

www.twitter.com/cf-newa

www.newaethiopia.org

ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት - ኢትዮጵያ

## "በግጭትም ሆነ በሰላም ወቅት ፆታዊ ጥቃት ይቁም ! "
## ዝም አንበል !

### የዚህ ዓመት ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት

16ቱ የንቅናቄ ወቅት በዓለም አቀፉ የሴቶች አመራር ኢንስቲቲዩት (Center for Women's Global Leadership) እና ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች በተሰባሰቡ የሴቶች መብት ተሟጋቾች እ.አ.አ በ1991 የተጀመረ እንቅስቃሴ ሲሆን ከዚያ ወዲህ በመላው ዓለም የሴቶች ጥቃትን የማስቆም ጥሪ ለማድረግ ዓይነተኛ መንገድ ሆኖ ቀጥሏል። በየዓመቱም በሃገር አቀፍ ደረጃ ከህዳር 16 ዓ.ም (የሴቶች ጥቃት የመከላከል ቀን) ጀምሮ እስከ ታህሳስ 1 (የሰብአዊ መብት ቀን) ድረስ ባሉት 16 ቀናት ዘመቻ የሚካሄድ ሲሆን ሁለቱ ቀናት የተመረጡበት ዋና ምክንያትም በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ለማስቀረት እና የሰብአዊ መብት እሴቶች ቁርጠኝትን አፅንኦት ለመስጠት እንዲሁም የሴቶች ጥቃት ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ጥሰት መሆኑን ለማመላከትም ነው፡፡ የ16ቱ ቀን ንቅናቄ በዓለም አቀፍ ደረጃ ፆታዊ ጥቃቶችን ለማስቀረት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ማስተባበሪያ ስልት በመሆን ያገለግላል፡፡ ምንም እንኳን በተለያዩ አካላት የተከወኑ ተግባራት ፆታዊ ጥቃትን ለመቀነስ የራሳቸውን አስተዋፅኦ እያደረጉ ቢሆንም አሁንም በተለያየ ሁኔታ እና ቦታዎች ፆታዊ ጥቃት በሰፊው እየተፈፀመ እንዳለ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በዘንድሮውም የ16ቱ የንቅናቄ ወቅት ፆታዊ ጥቃት ይቁም ንቅናቄ በዓለም አቀፍ ደረጃ "UNITE: ACTIVISM TO END VIOLENCE AGAINIST WOMEN AND GIRLS" "ትብብር፤ በሴቶችና ሴት ህፃናት ላይ የሚደርስ ፆታዊ ጥቃትን ለማስቆም " በሚል መሪ ሃሳብ እንዲሁም በሃገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ "ሴቶችን እናከብራለው ! ጥቃታቸውንም እንከላከላለው ! " በሚል መሪ ሃሳብ ይከበራል፡፡

የዘመቻ ቡድኑ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ለይቶ በማውጣት ለሚመለከታቸው አካላት ጋዜጣዊ መግለጫን ጨምሮ በተለያየ መልክ ያሳውቃል፤ ይወተውታል፤በጥበብ ስራዎች፡ በመገናኛ ብዙሃንና በሌሎችም መንገዶች የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በመሆን ይወያያል፤ ግንዛቤም ይፈጥራል፤ መፍትሄ ያፈላልጋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚደርስ ፆታዊ ጥቃትን ለመከላከልና የሴቶች መብት እንቅስቃሴን ወደኋላ እንዳይመለስ የአጋሮችና የባለድርሻዎች ትብብር እንዲጠናከር ቅስቀሳ ማድረግ፣ የሴቶች መብት እንቅስቃሴዎች ድምፅን ማስተጋባት፣ በመንግሥታት፣ በግሉ ዘርፍ በተቋማትና በለጋሽ በሴቶችና ህፃናት መብት ላይ ለሚሰሩ ድርጅቶች ትርጉም ያለውና ዘላቂ የፋይናንስ ድጋፍ እንዲደረግ ጥሪ ማድረግ፣ የሴት መብት ተከራካሪዎች ከጥቃት እንዲጠበቁ ድጋፍና ከለላ እንዲያገኙ መወትወትና የሴቶች የውሳኔ ሰጭነትና የፖለቲካ ተሳትፎ አስፈላጊነትን ማሳሰብ ሌሎቹ የዘመቻው ትኩረቶች ናቸው።

## ጥቃት ምንድን ነው?

ጥቃት - በአለም አቀፍ የጤና ድርጅት (WHO) ማብራሪያ

በማብራሪያው መሰረት ጥቃት ማለት አካላዊ ሃይልን ወይም አቅምን በመጠቀም በራስ ላይ፣ በሌላ ሰው፣ በቡድን ወይም በማህረሰብ ላይ የሚፈፀም እና አካላዊ፣ የስነ-ልቦዊ ጉዳት ወይም ሞትን በተጨባጭ የሚያስከትል ወይም ሊያስከትል የሚችል የሰብዓዊ መብት ጥሰት ነው፡፡

ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት

ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት በተዛባ የሥርዓተ- ፆታ ግንዛቤና አስተሳሰብ ምክንያት በተለያየ መንገድ በሴቶች፣ ህፃናትና በወንዶች ላይ የሚፈፀም ተግባር ሲሆን በሁሉም ፆታና እድሜ ክልል ላይ ባሉ ግለሰቦች እና የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ሊፈፀም የሚችል ቢሆንም በብዛትና በስፋት በሴቶች ላይ ስለሚፈፀም ፆታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ተብሎ ይጠራል፡፡

ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት-ኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት መሪነት የሚሰባሰበው "ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት-ኢትዮጵያ" ከ2006ዓ.ም ጀምሮ በሃገር አቀፍ ደረጃ ፆታዊ ጥቃትን ለመቀነስ ብሎም ለማስቆም የተለያዩ ተግባራት ሲከናወን ቆይቷል፡፡ ቡድኑ ሰብዓዊ መብት በተለይም የሴቶች መብቶች ላይ የሚሰሩ አዲስ ሲቪክ ተቋማትን፣ መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ የሚመለከታቸው የተባበሩት መንግሥታት ኤጀንሲዎችን በመጨመር የአባላቱን ቁጥር ከፍ እያደረገ መጥቷል።

ቡድኑ በ16ቱ የንቅናቄ ወቅት የሚታሰቡ ቀናትን በጋራ በማክበር፣ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ለይቶ ጋዜጣዊ መግለጫ በመስጠት፣ የጥበብ ስራዎችን ጨምሮ የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮችን በማዘጋጀት፣ የግፊት ስራዎችን ለመስራት የሚያስችሉ የምክክር እና የውይይት መድረኮችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆኖ ያዘጋጃል። ዘመቻው ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸውንም በተለያየ መንገድ ይዘክራል። በዚህ ዓመትም ዘመቻው በግጭት ወቅት ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶችና ታዳጊዎች የስነልቦና ድጋፍን ጨምሮ ሌሎች እገዛዎችን ማግኘት በሚችሉበት መንገድ ላይም ይመክራል።

በ16ቱ ቀናት ዘመቻ ፆታዊ ጥቃት ይቁም የሚታሰቡ ቀናት

- ህዳር 16 ዓለም አቀፍ የነጭ ሪቫን ቀን
- ህዳር 20 ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተከላካዮች ቀን
- ህዳር 22 ዓለም አቀፍ የኤድስ ቀን
- ህዳር 24 ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀን

ህዳር 27 ዓለም አቀፍ የጥቃት ሰለባዎች ቀን

ታህሳስ 1 ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ቀን

የዘመቻ በፆታዊ ጥቃት-ኢትዮጵያ አባላት



- የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት
- የኢትዮጵያ ሴት አካል ጉዳተኞ ብሄራዊ ማህበር
- የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያ ሴቶች ማኅበር
- የሴቶች ይችላሉ ማህበር
- አዲስ አበባ ሴቶች ማህበር
- የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር
- ፋሚሊ ሰርቪስ አሶሴሽን
- መጀጀጉዋ ሎካ የሴቶች ልማት ማህበር
- ሲቁ የሴቶች ልማት ማህበር
- የኢትዮጵያ ሰራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽ
- ሳራ ፍትህ ከሁሉም
- ሴታዊት
- የሴቶች ማረፊያ እና ልማት ማኅበር
- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን
- የወጣት ሴቶች ብሄራዊ በጎ አድራጎት ድርጅት
- ዩኤን ውመን
- አክሽን ኤይድ
- ኒው ሚሊኒየም ውመን ኢምፓወርመንት ኦርጋናይዜሽን
- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ማዕከል
- የተባበሩት መንግስታት የምስራቅ አፍሪካ የሰብዓዊ መብት ጽ/ቤት
- የኢትዮጵያ ሴቶች መብት ተሟጋች



"የዘመቻ በፆታዊ ጥቃት-ኢትዮጵያ" አባላት ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ቢሆኑም አባላቱ ከተለያዩ መንግስታዊና፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ተቋማት እንዲሁም ክልሎች የሲቪክ ማህበራት ጋር በመተባበር የ16ቱን ቀናት ንቅናቄ ያኪያሂዳሉ፡፡

"ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት ኢትዮጵያ" አባላት አገሪቱ እያለፈች ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት አገራዊው መሪ ሃሳብ "በግጭትም ሆነ በሰላም ወቅት ፆታዊ ጥቃት ይቁም!" ዝም አንበል! እንዲሆን ተስማምቷል። ቡድኑ የንቅናቄው አገራዊ መሪ ሃሳብ ይዘት ይህ እንዲሆን የወሰነው በአገሪቱ ከሁለት ዓመታት በላይ በዘለቀው የሰሜን ኢትዮጵያ ግጭት፤ በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች በተቀሰቀሱ ግጭቶች ሴቶችና ህፃናት ግንባር ቀደም ተጎጅዎች በመሆናቸውና ሰብዓዊ እርዳታ ከሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት እነሱ በመሆናቸው ነው። ስለዚህም መሪ ሃሳቡ የተመረጠው በግጭት ወቅት የፆታዊ ጥቃት ተግባራት በቂ የህግ ምላሽ እንዲያገኙ፣ማድረግን በማሰብም የተመረጠ መሪ ሃሳብ ነው።በተባበሩት መንግስታት ድርጅት በጦርነት ወቅት የሚፈፀሙ ፆታዊ ጥቃቶችን የሚመለከተው ክፍል ተወካይ የሆኑት ፕራሚላ ፓተን በሰሜን ኢትዮጵያው ግጭት በርካታ ሴቶች ላይ ፆታዊ ጥቃት መፈፀሙን አስመልክቶ ሲናገሩ "ፆታዊ ጥቃት ያልታሰበ ጥፋት( ጉዳት) እንዲሁም የማያስቀሩት የጦርነት የጎንዮሽ ውጤትም አይደለም" ብለዋል፡፡

"ዘመቻ በፆታዊ ጥቃት- ኢትዮጵያ" በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረገውን እንቅስቃሴ እና መሪ ሃሳብ በእጅጉ ይደግፋል፡ ከዚህም በተጨማሪ በሃገራችን ያለውን አለመረጋጋት እና ግጭት በዚህም ሳቢያ በሴቶች ላይ እየደረሱ ያሉ ፆታዊ ጥቃቶችን ታሳቢ በማድረግ "በግጭትም ሆነ በሰላም ወቅት ፆታዊ ጥቃት ይቁም!" ዝም አንበል! በሚል መሪ ሃሳብ ከባለድርሻ አካላት ጋር በአንድ ላይ ያከብራል፡፡